**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)**
**Ethiopian Peoples Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)**

# ወያኔ አሸባሪነቱን እባብ ተናዳፊነቱን አይተውም!

ሚያዝያ 20 2010 ዓ.ም

የወያኔ ፍጹም እምነትና ተልዕኮ ምን እንደሆነ ለማያውቁ እንዲያውቁ ለሚያውቁም እንዲያገናዝቡ ቀደም ብሎ ተደጋግሞ ቢነገርም ይህ ዘረኛ ቡድን የተካነበትን የማጭበርበሪያ ስልት በቅጡ የተረዳው ቁጥር ሰፊ እንዳልነበረ ይታወቃል። ለ27 ዓመት ሰላምን ከምድሪቱ ያጠፋ፣ ኢትዮጵያን የጨለማ ማቅ ያለበሳት፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቿን አስሮ ለጆሮ በሚዘገንን ግብረ-ስየል አሰቃይቶ ከሰውነት ውጭ እንዳላደረገ፣ በሺዎቹ የሚቆጠሩትን ዜጎችን ህይዎት ልዩ ነብሰ ገዳይ ቡድን አሠማርቶ (በስደት ዓለም የነበሩም ጭምር) እንዳላጠፋ፣ ዜጎች መብታችን ይከበር፣ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ፣ አትከፋፍሉን፣ የትግሬ የበላይነት ይቁም፣ በሃይማኖታችን ጣልቃ አትግቡ፣ ድምጻችን ይሰማ በማለት ሰላማዊ ሰልፍ ስለወጡ የአሸባሪነት ታፔላ እየለጠፈ ወደ ማጎሪያዎቹ እንዳላጋዘ፣ የሕዝብን የዜግነት መብት ረግጦ ስንቱን አማራ ለፍቶ ከሠራው ቦታ አፈናቅሎ እንደናዚዎቹ በገፍ እንዳላጋዘና እንዳልጨፈጨፈ፣ አሁንም ይህንን ፋሽስታዊ ድርጊቱን በወታደራዊ እዝ አጠናክሮ ዜጎችን እየፈጀ ያለና አገርን ሠላም ያሳጣ አረመኔ አገዛዝ፣ ከሰሞኑ እያስደመጠ ያለው የሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲ ዲስኩር ከዚሁ አገዛዝ ሲሰማ ጆሮ የሚያደማ ብቻ ሳይሆን ለህዝብ ያለው ንቀት የደረሰበትን ደረጃ አጉልቶ የሚያሳይ ነው።

ወያኔ ሰላም ሲል፡ ህጋዊ አሠራርና ተጠያቂነትን ከስር መሠረቱ ነቅሎ ጥሎ በቦታው ሙስናን መተካት፣ አገርን ለባዕዳን መሸጥ፣ ሕዝብን እርስ በርስ ማጫረስ፣ በአማራው ላይ የጀመረውን የተቀነባበረ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ማፋጠንና ይህን የሚጠይቁትን የአገሪቱ ዜጎች በገፍ መግደል፣ አስሮ ማሰቃየት፣ አፍኖ ማጥፋና ተቃውሞው ከረር ሲልም ሙሉ በሙሉ በሚቆጣጠረው መድረክ ትግሬዎች ተጠቃን ብሎ ጎጥ ላይ መንጠላጠል ያደገበት ባህሪው ነው። አሳዛኙ እውነታ ግን ይህ ዘረኛ ጥሪው አልሠራለትም ለማለት የሚያበቃ እስካሁን ምንም ፍንጭ አለመታየቱ ነው። የሀገሪቱን መደበኛ የመከላከያ ሠራዊት በትኖ በቡድን ጥቅም አስጠባቂ ጦር አገሪቱን አግቶ የቀጠለ ፋሽስታዊ አገዛዙን ዜጎች አሜን ብለው እንዲቀበሉ በወታደራዊ አዋጅ የተደገፈ ሽብር እያካሄደ ነው። ወትሮም ቢሆን ሰላም ማለት ለወያኔ፣ ስብሰባ ጠርቶ በውድቅት ሌሊት አጋድሞ ማረድ፣ ምሳ ጠርቶ በመርዝ መግደል፣ እልቂት አድርሶ እርቅ መጥራት፣ አንቆ ገሎ ወንጀለኛውን መፈለግ ውዘተ አብሮት የተፈጠረ ባህሪው መሆኑን የዘነጉ ብዙዎች የዚሁ አረመኔ ቡድን ሰለባ ሆነዋል።

ስለሆነም ወያኔ ሰላም፣ አድገት፣ መልካም አስተዳደር፣ ዲሞክራሲ ወዘተ በሚል ባዶ ቃላት ለማጃጃል የሚጥረው በሕዝብ እና በሀገር ላይ ጦርነት እውጆ ነው። ይህንን ወያኔያዊ ቀልዱን እንደ ፖሊሲ ለመደስኮር በጠራው ስብሰባ ሕዝብ ዝቅጠቱን በግልጽ እየነገረው እንኳን መልዕክቱን ሳይሆን መልክተኛውን ለማጥፋት ከማሴር ሌላ እንዳያስብ በቀልና ትዕቢት ልቡን ደፍኖታል። ወያኔ ሰላም ሲል በአገርና በህዝብ ላይ እያሾፈ መሆኑን ለመገንዘብ በአሁኑ ሰዓት በብዙ ሺህ ወገኖቻችን ላይ

Tel: 202-291-5832 5309 Georgia Ave. NW 2nd Fl. Washington DC 20011

E-mail: eprpylnew @gmail.com Website: www.eprpyl.com

ግድያ፣ አፍኖ ወስዶ የደረሱበትን ማጥፋት፣ በየማጎሪያዎቹ ማጋዝ፣ በግብረ-ስየል ማሰቃየትና ብዙ ብዙ ፋሽስታዊ ግፍን በመፈጸም ላይ ነው። የሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ስርጎ ገቦችን ሰግስጎ እምነትን በማራከስ ላይ ነው። ዋልድባን የመሠሉ ጥንታዊ የሃይማኖትና የታሪክ ተቋማት ውስጥ ቅጥረኞችን በማሰማራት መነኩሴዎችን አዋክቦ እያባረረ ሲሆን፣ ገዳሙንም በማፍረስ ላይ ነው። ብዙ ሰቆቃ ካደረሰባቸው በኋላ በህዝብ ትግል ሰሞኑን የፈታቸው የዋልድባ የሃይማኖት አባቶች "አልተፈታንም ከትንሹ እስር ቤት ወደ ትልቁ እስር ቤት ነው የተዘዋወርነው፤ ተፈታን የምንለው አገራችን ቤተክርስቲያናችን ስትፈታ ነው።" ያሉት ወያኔ የሚባል ዘረኛ አገዛዝ በህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ግፍ ምን ደረጃ ላይ እንንደደረሰ አመላካች ነው።

በወያኔ መዝገበ ቃላት ዕድገት ማለት፡ ሌላ ሳይሆን ከበራሪ ሌብነት ወደ ተደራጀ ሌብነት መሸጋገር ማለት ነው። ኤፈርት፣ ሜቴክ፣ ትልማ ወዘት በሚባሉት የዘረፋ መረቦቹ የመላው ኢትዮጵያን ብሄራዊ ሃብት ከወያኔ ባለስልጣናትና የቤተሰቦቻቸው ቅርምት አልፎ የትግራይ ምርጦችን ለመፍጠር የዘረፋውን መረብ ይበልጥ መግፋት ማለት ነው። ወያኔ ተራ ወንበዴ መሆኑን ያስመሰከረው ገና በለስ ቀንቶት አዲስ አበባን በረገጠ ሰሞን ነበር። አሉ የተባሉ የሃገሪቱን ተቋሞች ዘርፏል። ከጣና በለስ ብዙ አይነት መሳሪያዎችን፣ የዳቦ መጋገሪያዎችን ከአዲስ አበባ፣ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ጀኔረተሮችና የኤሌክትሪክ ምሰሶዎች ከጎንደር፣ ወልዲያና ባህርዳር ወዘተ ህዝብ ነጥቆ ወደ ትግራይ ሲያግዝ ነበር። ስለ ወያኔ የዘረፋ መረብ እዚህ ላይ ለማንሳት መሞከር አባይን በጭልፋ ቢሆንም፣ በጨረፍታ ለመጥቀስ ያህል፣ ከብዙ የኤፈርት ግዙፍ ኩባንያዎች አንዱ የትግራይ አልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካን ለማስፋፋትና ገበያውን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር እንዲችል በወያኔ ትዕዛዝ የንግድና የልማት ባንኮችን በማይመለስ ብድር አራቁቷል፣ የመከላከያ ሚኒስቴርም ለወታደር የደንብ ልብስና እንዲሁም ሌሎች የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን አስገድዶ የሸቀጡ ደንበኛ ከማድርግ ጀምሮ፣ የአቃቂ፣ አርባምንጭ፣ አዋሳ፣ ድሬዳዋና ሌሎችም ቦታዎች ያሉ የሀገሪቱ ፋብሪካዎችን በተቀነባበረ ሴራ እንዲዳከሙ አድርጓል። የነዚህ መስሪያ ቤት ሠራተኞም ብዙዎች ከስራ ውጭ ሆነው ከነቤተሰቦቻቸው መንገድ ላይ ወድቀዋል። ወያኔ ልማት የሚለው ይህን መሰሉን የተደራጀ ውንብድና ነው። ሁሉም ነገር ወደ ትግራይ ማለቱ ነው። ትግራይ እንድትለማ ኢትዮጵያን እናድማ ማለቱ ነው፣

ሰላም ሲልም እንደዚሁ ከበስተጀርባ የትግራይ-ትግሪኝ ሴራ እያጠነጠነ ነው። ለወያኔ የሰላም ትርጉሙ ኢትዮጵያን በዘረኛ መቅሰፍቱ እስኪያጠፋት የስልጣን ዘመኑ መራዘም ብቻ ነው። ወያኔ ጊዜ ለመግዛት ባቀነባበረው የአዲስ ጠቅላይ ሚኒስቴር ድራማውም ተመስጠው አዲሱን ጠ/ሚ የኢትዮጵያ ስርየት ሲሉ የተደመጡም ጥቂት አይደሉም። ስለዚህ ነው ከሩብ ምዕተ ዓመት የሀገር ውድመት በኋላ በተለመደው የወያኔ ረዥም የውሸት ምላስ ተሳክሮ የሃሴት ከበሮ መደለቅ እብደትን ያካልላል። አለዚያም ወንጀል ነው የምንለው።

ወያኔ የዛሬውን ብቻ ሳይሆን መጪውን ኢትዮጵያዊ ትውልድም የመኖር ዋስትና አሳጥቷል። ያንኑ ዘረኛ አገዛዙን ለማስቀጠል አዲስ ዩኒፎርም አልብሶ ባሰማራው ግለሰብ በኩል ከሚያስደምጠው ሁኔታማ የአገር ሀብት ብቻ ሳይሆን መልካም ፅንሰ ሃሳብም ከዘረፋው አላመለጠም ማለት ይቻላል። አንድነት፣ ኢትዮጵያዊነት፣ መልካም አስተዳደር ወዘተ እያለ በማንኛውም ግምት ከተፈጥሯዊ ባህሪው ጋር ዝምድና የሌለው ባዶ ቃላት የሚያዥጎደጉደው በአንድ ታሪካዊ አደጋ ቤተመንግስት የገባ ወሮበላ መሆኑን የደበቀ እየመሰለው ነው። ይህ ሃቅ እንዳለ ሁኖ ግን "የአካለ ጎደሎ አሽከር አጎንብሶ ይራመዳል" እንዲሉ፣ አገራችን ከአዜብ እንጀራና ከጊዜ እንስጣቸው ሳይጠሩ አቤት ተማርን ባይ ሆዳሞች ከድርሻዋ በላይ እስካሏት ድረስ አገዛዙ አድሜውን ለማራዘም ከፍተቶችን ማግኘቱ የታየና አሁንም እየታየ ያለ ነው።

ምንም እንኳን መቶ በመቶ በተራ ትዕቢት የተወጠሩ ወያኔዎች ይሆነናል ብለው ባዘጋጁት ግለሰብ በመጠቀም የህዝብን ድምጽ ሊነጥቁ (ሊያሽመደምዱ) ቢሞክሩም፣ ገና መቀሌን ሲረግጥ "የወርቅ ዘሮች" በማለት የሟች አለቃው ግልባጭ ሆኖ ተገኘ። በመሆኑም የፈለገ ካባ ለባሽ ቢቆም ወሳኙ ወያኔ መሆኑን ሊያዘናጉ ለተነሱት ሆዳሞችና አንጃዎች በማያወላዳ ቋንቋ አሳወቃቸው። ከወያኔ በላይ ስልጣን ያለው ጠ/ሚ ከራሱ ከወያኔ አገዛዝ ይወጣል ብሎ ማመን ቢያንስ የፖለቲካ ክስረት ነው። አለዚያም ጭልጥ ያለ አድርባይነት ነው።

ወያኔ ለ 27 ዓመታት አገሪቱን የሚመሩ ዜጎቿ በፖለቲካ ፍልስፍናቸው ወይም ሀገራዊ ራዕያቸው ሳይሆን በጎጣቸው ወይም የዘር ሃረጋቸው መመዘኛ እንዲሆን የፖለቲካውን አየር በመመረዝ የራሷን የሀገሪቱን ንብረት በመጠቀም መጥፊያዋን ሲያመቻችበት ቆይቷል። ሆኖም ግን በ2008 ዓ.ም. አገራቸውን ወያኔ ካሰራጨው ቀሳፊ በሽታ ለመታደግ የተነሱ አስተዋይ ዜጎቿ ታግለው ወያኔ ላሰራጨው ዘረኛ ተስቦ ማርከሻውን አገኙበት። የዘራው አሜካላ አፍርቶ (ኢትዮጵያዊያን በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ ወዘተ ተከፋፍለው እርስበርስ የማጫረስ ዓላማውን ስኬት) ለማየት የቋመጠው ወያኔ የሚይዘው የሚጨብጠው አጣ። ብዙ ሳይቆይ መገለባበጥ ተፈጥሮው ነውና ሴራውን ህዝብ እንዳከሸፈበት ሲገነዘብ፣ ነባር ካድሬዎቹን "ቋንቋቸውን" እንዲቀይሩና ህዘቡ የሚናገረውን እንዲናገሩ፣ ብሶቱን ብሶታቸው አስመስለው እንዲቀርቡ፣ መስማት የሚፈልገውን አንድነትና ኢትዮጵያዊነት እንዲያስተጋቡ፣ የፈለገው ሰው ለማስመረጥ ያደረገው ሙከራ ከቁጥጥሩ ውጪ እንደሆነና እቅዱ እንደተሸነፈበት ወሬውን ሆን ብሎ በማሾለክ፣ ከገባበት አጣብቂኝ ሁኔታ ለመውጣት ይጠቅመኛል ብሎ ያዘጋጀውን ምልምል ጠ/ሚ አደረገ።

ይህ ነበር የጭዋታው ቅንብር። የሆነውም ይኸው ነው። ወያኔ ልደቱን (ከህደቱን) አንድ ወር አስሮ ሲፈታ ማንዴላ ያሉት ጉዶች አሁንም ሳያፍሩ የወያኔውን የደህንነት ሠራተኛ ኮሎኔል የኢትዮጵያ መድህን አድርገው ሊያጃጅሉን በመሯሯጥ ላይ ናቸው። በውጪው ዓለምም እንዲሁ ለንደን ላይ ተገንጣዮችን ሰብስቦ ያነገሰብን የባዕድ አገር ሰው፣ ድጋፍ ስጡት ሲል መደመጡ በራሱ አነጋጋሪና የማይታዩ እጆች የሰው ኪስ ውስጥ መያዛቸውን አመላካች ነው።

ከሃያ ሰባት ዓመታት የመከራ ዘመን በኋላ በወያኔዎቹ አጭበርባሪ ድራማ የሚወናበድ ኢትዮጵያዊ ከአገዛዙ ጋር ተጣብቆ ተጠቃሚ የሆነው ክፍል ብቻ ነው ማለት ይቻላል። በዘረኛ አምባገነኖች የደቀቀችና በወርባላ የወያኔ ካድሬዎች አስተዳደር የዳሸቀችን ሀገር መልሶ ለማቋቋምና ለመገንባት ሕዝብ በአንድ መንፈስ በአንድ ድምጽ ተባብሮ መነሳቱ ሰላስደነገጠው ፈላጭ ቆራጭነቱን ለማስቀጠል ቋምጦ ህዝብን ለመከፋፈል በማን አለብኝነት አሁንም ሊፈነጭብን የቀን-ጅብ ሰርጎ ገቦችን አሠማርቷል። በተጨማሪ በተቃዋሚ ስም የሚያገለግሉ ድርጅቶችንና ግለሰቦችንም እንዲሁ በሥፋት አሠማርቶ በማንቀሳቀስ ላይ ነው።

ስለሆነም ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው፣ ወያኔ ዛሬ የሀገር ሰላም ፈላጊ መስሎ ሙሉ በሙሉ በሚቆጣጠረው የብዙሀን መገናኛ ሲያላዝን መስማት የጦር መሳሪያ የሚያመርት ኩባንያ ስለ ዓለም ሰላም ሲሰብክ እንደመስማት ነው ። ወያኔ ገና ጫካ እያለ ኢትዮጵያዊነትን ኢላማ አድርጎ በመነሳቱ ከኢትዮጵያዊያን ጋር ያኔውኑ ደም ተቃብቷል። ወያኔ ሰላም ድርድርና ሥልጣንን የመጋራት ተፈጥሯዊ ባህሪው ስለማይፍቅድለት የተለየ ሀሳብና ራዕይ ያላቸውን ግለሰቦች፤ ቡድኖች፤ ተቋማትና የፖለቲካ ድርጀቶችን በጠመንጃ ሃይል በማስወገድ፤ በመከፋፈልና በማጥፋት የተካነ ፤ ኢትዮጵያን በመበጣጠስ በርስበርስ ጦርነት ማጥ በመከተት የሥልጣን እድሜውን ለማራዝም የፈለገ ዘረኛና አሸባሪ ቡድን ነው። ወያኔ ትግራይ ትግሪኝ የሚለውን ቅዠቱን ተግባራዊ ለማድረግ ውስጥ ለውስጥ ከሚካሂዳቸው እንቅስቃሴዎቹ አሻራ ይታያል። ወያኔ በህዝብ አመጽ በተወጠረና በተገፋ ቁጥር የትግሬነት ካርዱን ከፍ እያደረገ ካድሬዎቹን ያዘምራል። ወያኔ የህዝብን ምክር የሚሰማ ልቦና ስለሌለው ደደቢት ላይ ያደቆነው ሰይጣን እያሰጓራ እዚያው ወስዶ እንደሚቀብረው በረካታ ምልክቶችን እያየን ነው። ወያኔ በንጹሃን ደም ጨቅይቷል።

ወያኔ ከሰረ መሠረቱ የተበላሸና የዘቀጠ በመሆኑ በአወደ ጉባኤ፤ በምክር፤ በምለላ በሽምግልና፤ለመሻሻልና ለመለወጥ መጣር ከንቱ መሆኑን ዛሬም ያልተረዱ መኖራቸው ይታያል። የወያኔ መሪዎች ዛሬም በአለቀ ሰዓት ለ 27 ዓመታት ያካሄዱትን የአገር ሀብት ዘረፋ ተግባራቸውን አብዮታዊ ዲሞክራሲና ልማታዊ መንግሥት በሚል የደንቆሮ ለቅሶ... አልቀየሩም። የደነቆሩበት ፀረ- ሀገረና ፀረ-ህዝብ ርእዮታቸውን የሚተችና የሚቃወመውን ሁሉ ያሽማቅቃሉ፤ በአድህሪነትና በጸረ ትግሬነት ይወነጅላሉ። በደደቢት በረሀ የደቆኑበት መለያቸው የሆነው ህዝብን የመናቅ መንፈስ ሁሌም ወደ ሃይልና ጭካኔ ይመራቸዋል። ወያኔ በተፈጥሮው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተነሳ አንዳች መርገም በመሆኑ "አፍን!"፤ አግድ!"፤ አሸብር!፤ ግደል!"ን እንዲያዘወትር አድርጎታል። ወትሮስ ቢሆን ወያኔ የቆመው የባእዳንን ጥቅም ለማስጠበቅ እስከሆነ ድረስ ለኢትዮጵያውያን በጎና ለአገራችን መልካም እይታ እንዲኖረው ለምን ይጠበቃል።

መጽሐፈ ወያኔ ሲገለጥ ከፈፍለህ አጥፋ በመሆኑ ከቀድሞዎቹ አምባገነኖች ፍጹም ይለያል። የወያኔ ዓላማው ኢትዮጵያን ከፋፍሎና ዘርፎ ረግጦና አፍኖ መግዛት በመጨረሻም አዳክሞ መበታተን ነው። ይህ የወያኔ ዓላማ ደግሞ ባእዳኑን ዳንኪራ

ያስረገጠ መሆኑ አያጠራጥርም። እንዶድ በገርነቱ ውሃ ወሰደው ነውና በዚህ መፋዘዝ መዘናጋት የሀገርን ጥፋት የሚያስከትልና የወያኔን የሥልጣን እድሜ የሚያራዝም በመሆኑ የአገዛዙን መሰሪ ተልዕኮ ጠንቅቆ መረዳት ወሳኝ ነው።

የወያኔ ሰላም በሞቃዲሾ ከሰፈነው "ሰላም" በመሠረቱ ያልተለየ ነው። ዛሬ መላው የአገሪቱ ክፍሎች በወያኔ የፀጥታና የአጋዚ ጦር እየታመሱ ነው። ጎጃምና ጎንደር በዘመነ ደርግ የቆጠሩትን ፍዳ ዛሬም እጅግ በከፋ ሁኔታ እየኖሩት በወያኔ ጦር እየታመሱ ናቸው። ሐረርጌ፣ ሸዋ፣ ባሌ፣ አርሲ፣ ወለጋ፣ ወሎ፣ ሲዳሞ ወዘተ... ሁሉም ወያኔያዊ "ሰላም"ን" ተቀዳጅተዋል። ሰላም የጦርነት መወገድና የፍትሃዊ አስተዳደር ውጤት ማለት እስከሆነ ድረስ በኢትዮጵያ ሰላም የለም። ወያኔና ሀቅ የሰማይና የምድርን ያክል የተራራቁ በመሆናቸው ይህን ሊገነዘብ አይጠበቅም ። ወያኔ በሸራተን አዲስ በጠራው "የሰላም ጉባኤ" ተብየው ላይ ሕዝብ ብሶትና ስጋቱን በመደጋጋፍ በአንድ ድምፅ በአደባባይ ከፍ አድርጎ አስተጋብቷል።

" ሀገርና ህዝብን የምታበጣብጡ እናንተው (ወያኔዎች) ናችሁ! ኮማንድ ፖስት የምትሉት ሰላምን አያስፍንም! የተከፋና የተቆጣን ሰማንያ ሚሊሆን ህዝብ በወታደር ሃይል ማስቆም አይቻልም " ወዘተ። የምትሰሙ ከሆነ ሁሉንም የፖለቲካ እስረኞች ፍቱ፣ ከሁሉም የኢትዮጵያያን ተቃውሚ ሃይሎች ጋር ተነጋገሩ፣ በቅድሚያ በራሳችሁ ውስጥ ሰላምን ፍጠሩ፣ ከኢትዮጵያዊነት ጋር ታረቁ፣ በብሄር አትከፋፍሉን፣ ወጣቱ የሚሰደደውና በየበረሃውና በየባህሩ ህይወቱን የሚያጣው ከአገዛዙ የተሻለ ነገርና ተስፋ በማጣቱ ብቻ ነው ወዘተ " የሚሉ ነበሩ። ይህ በህዝብ ሁሉ የታወቀ ሀቅ የወያኔን ዓላማና ተግባር ከኢትዮጵያ ጥቅምና ከሕዝቦቿ ፍላጎት ጋር ፍፁም የማይታረቅ መሆኑን ያረጋግጣል። ወያኔ ለሰላም ቆሚል የሚሉ ካሉ፣ የአባትህ ቤት ሲዘረፍ ... አይነት ተጠቃሚ ወይም የሰላምን ትርጉም የሳቱ መሆን አለባቸው። በወያኔ የግፍ አገዛዝ የታፈነውና የተረገጠው ሕዝብ በአደባባይ ወያኔ ባዘጋጀው በራሱ መድረክ ያልፍርሃት ሀቁን እየነገራቸው ነው። ወያኔ ለኢትዮጵያ ያስባል የሚባል ከሆነም በገቢር ሲፈተን የደረበው የዴ፤ዴ ፤ዴዎቹ ካባ ሲገለጥ ዛሬም የትንናቱ የጥንቱ የጥዋቱ ወንበዴ ነው። ወያኔ ወያኔነቱን አልተወም። በሽታውን ምክርም ፤ ህክምናም ጠበልም የሚያድነው ሆኖ አልተገኘም።

የወያኔ መሪዎች ተልዕኮ፣ ዓላማና አመጣጥ አገርን ለመዝረፍና አገርን ለማፍረስ ነው። ህብረ-ብሄራዊ ኢትዮጵያን ለማስተዳደር የሚያስችል ኢትዮጵያዊነት በደማቸው የለም። ወያኔ በአምባገነንትና በአንድ ጎጠኛ ፓርቲ (በአውራ ፓርቲነት) ሥርዓት ላይ ያለውን እምነት ለማስቀጠል የወታደሩንና ጸጥታ ህይሉን አጠናክሮ እንደያዘ ለመቀጠል ያለውን ፍላጎት በተግባር እያረጋገጠ ይገኛል። መለስ በሃይለማርያም፣ ሃይለማሪያም በአቢይ፣ አቢይ በደመቀ ወይም በሽፈራው ቢተካ የፖለቲካ ሥልጣን ሕዝብ ባልመረጠው ፓርቲ እጅ እስከተያዘ ድረስ ሕዝብ የተዋደቀለትና ክቡር ህይወቱን የገበረለት መሠረታዊ ለውጥ ( በነፃ የመደረጀት፣ ሀሳብን በነፃ የመግለጥ፣ የመሰብሰብ፣ የመቃውም የመምረጥና የመመረጥ) በአጠቃላይ የሕዝብ የሥልጣን ባላቤትነት አእስካልተረጋገጠ ድረስ ዴሞክራሲ አለ ተብሎ ቢዘፈንም ሀቁ የሚያሳየው ዘረኛ አምባገነነትን ነው።

የወያኔ ከፋፍለህ አጥፋ ፖሊሲ በሁሉም ፈርጅ መቀጠሉ አይቀሬ ነው ። ወያኔ ለአፍታም የሚታመን አይደለም። ወያኔ በሕዝብ አመጽ ተወጥሮ መውጫ ባጣበት የመጨረሻው ሰዓት ከኢትዮጵያ ህዝብ ከመታረቅና ህዝብን ይቅርታን ከመጠየቅ ይልቅ ከኢህአዴግ ምክር ቤት ስብሠባ በኋላ የሮጠው ክልሌ ወደሚለው ጎጡ ነው። ጎጠኝነትና ወያኔ የሚለያዩት ወያኔ ወደማይቀርለት መቃብሩ ሲወርድ ብቻ ነው።

ወያኔ ተልኮው ዝሆን ተሸክሞ ተራራን መውጣት ሆኖበታል። ከብዶታል ስለከበደው ማንነቱ የሆነውን ጎጠኝነት ይተዋል ይለወጣል ማለት አይደለም። ይፍጨረጨራል። ይተራመሳል። ያተራምሳል። የክፍፍል ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ በሚያደርገው መተራመስ ሀገርና ሕዝብን  እንዳያጠፋ ሕዝቡ በኅብረት ሊታገለው ይገባል ። አምባገነነትን መታገል ፍትሐዊ ነው። ሀገር አጥፊን ሀይል መቋቋም የዜገነት ግዳጅ ነው። የወያኔ አፍራሽ ዓላማ በተባበረ ሕዝባዊ ትግል መመከት አለበት። የትግል ሥልት ባለው ተጨባጭ ሁኔታ እንጂ በወያኔ አዋጅ የሚወሰን አይደለም።

ወያኔ ተፈጥሮው በኢትዮጰያና በሕዝቧ ጥላቻ ታውሮ ሰላም ያጣ ቡድን ነው። ወያኔና ሰላም ውሃና ዘይት ናቸው። ለወያኔ ሰላም ማለት አገርን ሲዘረፍ፣ ሕዝብንም እርስበርስ ሲያፋጅ፣ ንጹሃን ዜጎችን ሲያስርና ሲገድል፣ በብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ተረማምዶ የአንድ ዘር የበላይነትን ሲያራምድ፣ አማራው ላይ የዘር እልቂት ሲያደርስ፣ ለትግሬ የበላይነት የኢትዮጵያን ሲያወድም። ሰላም ነው፣ ስለዚህ አርፋችሁ ፀጥለጥ ብላችሁ ተገዙ ማለቱ ነው። ለ 27 ዓመት በህዝብና በሀገር ላይ የወያኔ ዘረኞች ያደረሱት በደል ሲታሰብ የጣለያንን ሽንፈት ለመበቀል የተነሱ ቅጥር ወራሪዎች እንጅ ሌላ ሊሆኑ አይችሉም። ይህንን የደደቢት አርዌ ደግፈው ኢትዮጵያን ወደ ባሰ ውድቀቷ እንዲገፋት ለዚህ ወይም ለዚያ ወያኔ ሠራሽ ድራማ ጊዜ አንስጠው በሚል ሳይጠየቁ ተባባሪ የሆኑትን ሁሉ ከወያኔዎቹ ባልተለየ ውግዝ ልናረጋቸውና ከሁሉም ማህበራዊ ህይወታችን ልናገላቸው ይገባል።

ትክከለኛ ሰላም የሚመጣው ሰላም ካሳጣን ወያኔ ሳይሆን፣ ይህ ሀገወጥ አገዛዝ ሙሉ በሙሉ ተወግዶ የህዝብን አዎንታ ያገኘ፣ አብዛኛው የሚገዛበትና የአናሳው መብት የሚጠበቅበት፣ የመንግስትን ስልጣን የሚወስን፣ ለመሠረታዊ መብቶች ዋስትና የሚሰጥና በህግ ፊት እኩልነትን፣ ነፃና ፍትሃዊ የሆነ የምርጫ ህግን የሚያስከብር፣ የህዝብ የሆነ ሕገ መንግስት የምትደተዳደር ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ ምሥራታ የሚያመቻች ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግሥት ሲቋቋም ብቻ ነው። ይህ ተግባራዊ እንዲሆንና ትግላችን ይበልጥ እንዲጠናከር ዋነኛ የሀገር ጠላት ከሆኑት ውጪ ሁሉንም ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ያካተተ ሠፊና ዕውነተኛ ህብረት ለመመስረት እንዲቻል አሁኑኑ ተግቶ መንቀሳቀስን ግድ ይላል። ስለሆነም ዘረኛው አገዛዝ በጭሌ መሣይ ካድሬዎቹ ባዶ ጩኸት ጊዜ ገዝቶ አገሪቱን ጨርሶ ሳያጠፋ ላንዴና ለመጨረሻ በአንድነት ታግለን በማስወገድ ሀገርን ለማዳን የሚኖረን ዕድል ነገ ሳይሆን ዛሬ መሆኑን ኢወክንድ አጥብቆ እያሳሰበ በትግል ላይ ካሉ ወገኖቹ ጎን ተሰልፎ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ሁሉ እየከፈለ ይገኛል ።

Tel: 202-291-5832    5309 Georgia Ave. NW 2nd Fl. Washington DC 20011

E-mail: eprpylnew @gmail.com    Website: www.eprpyl.com

## የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)
## Ethiopian Peoples Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

የተጀመረው ሕዝባዊ አመጽ ተጠናክሮ ይቀጥል!

Tel: 202-291-5832 5309 Georgia Ave. NW 2nd Fl. Washington DC 20011

E-mail: eprpylnew @gmail.com Website: www.eprpyl.com